# የቤተክርስቲያን ታሪክ


<u>አዘጋጅ</u>
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
**ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል**




<u>አሳታሚ</u>
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
**ማኅበረ ቅዱሳን**

**አዲስ አበባ**
1993 **ዓ.ም**



www.eotc-mkidusan.org



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷአል፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡» 1ኛ ቆሮ. 15.20-21



«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና፡፡» ሉቃ. 1.49

www.eotc-mkidusan.org

## የአርእስት ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

3. **የቤተክርስቲያን ታሪክ** ........................................................ 72

- የቤተክርስቲያን አመሠራረት ........................................................ 75
- ዘመነ መናፍቃን ........................................................ 76

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ........................................................ 79

# የቤተክርስቲያን ታሪክ

ከማኅበረ ቅዱሳን የትምህርት ክፍል

## ቤተክርስቲያን ማለት፡-

በክርስቶስ ክርስቲያን የተባሉ ምእመናን በኅብረት የሚጠሩበት በመጽሐፍ ቅዱስ ጎልቶ የሚታይ የምእመናን ስያሜ ነው፡፡ ማቴ.16÷18፣ 17፡፡ የሐዋ.5÷11 20÷28፡፡ ኤፌ.5÷23-33፡፡

ምእመናን በኅብረት ሥርዓተ አምልኮአቸውን የሚገልጹበት፣ የሚጸልዩበት ምሕረትንና ይቅርታን ለማግኘት ፈጣሪያቸውን ደጅ ለሚጠኑበትና ለሚቆርቡበት ለቅዱስ መካን የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ የሐዋ.2-46፡፡ ቤተመቅደስ እየተባለ ሲጠራም ከብዙ ቦታ እናገኘዋለን፡፡

አንዱ ምእመን በራሱ ቤተክርስቲያን ይባላል፡፡ ይህም ቤተክርስቶስ እንደማለት ነው፡፡ /1ኛ ቆሮ 6÷19–20/

የአማናዊት ቤተክርስቲያን ትክክለኛ ትርጉም የሚገኘው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ መሆኑ ቢታወቅም የወንጌል አምሳልና መርገፍ በሆነች በኦሪት ጉልተው የሚታዩ ምሳሌዎችን ባጭሩ እንመለከታለን፡፡

ቤተክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ የሚገለጽባት እግዚአብሔር የሚመሰገንባት ናት ካልን ሥርዓተ አምልኮና ስብሐተ እግዚአብሔር መቼ ተጀመረ? የሚል ሐሣብ ሊኖር ይገባል፡፡

ሥርዓተ አምልኮ የተጀመረው እግዚአብሔር ፍጥረቱን እመ ኀበ አልቦ ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይኸውም፡፡ መላእክት ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ» እያሉ ፈጣሪያቸውን በማመስገን አምልኮአቸውን የሚገልጹ ስለሆነ አምልኮተ እግዚአብሔር በዓለመ መላእክት ተጀመረ ማለት ነው /ኩፋሌ.2-6-8/፡፡

ሰውም በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለፈጣሪው ይገዛ ነበር፣ ልጆችም ከአባታቸው ባገኙት መንፈሳዊ ጥበብ መሠረት የአምልኮአቸው መግለጫ የሆነ መሥዋዕት አቅርበዋል፡፡ ለዚህም የመጀመሪያዎቹ መሥዋዕት አቅራቢዎች የአዳም ልጆች መሆናቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን /ዘፍ.4-3/፡፡

በዘመነ ኦሪቱ ሥርዓተ አምልኮ ይፈጸምባቸው ከነበሩ የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሐመረ ኖኅ
2. ክህነተ መልከ ጼዴቅ



www.eotc-mkidusan.org

3. ቤቴል /ቤትኤል/
4. ደብረ ሲና
5. ደብተራ ኦሪት
6. ምኩራብ /ሲናጎግ/ ቤተመቅደስ

## 1ኛ. ሐመረ ኖኅ /የኖኅ መርከብ/

የሰው ልጆች በምድር ላይ እየበዙ በሄዱ ጊዜ እግዚአብሔርን በድለው ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው ማለት በሕገ እግዚአብሔር የሚመራ አንድ ጻድቅ ሰው ኖኅ ብቻ ነበር፡፡

ሰዎች በበደላቸው ምክንያት በማየ አይኅ /በንፍር ውኃ/ ሲደመሰሱ ኖኅ ግን ስምንት ራሱን ይዞ ወደ መርከብ ካስገባቸው እንስሳት አራዊትና አዕዋፍ እንደየወገናቸው ጋር ከጥፋት ድነዋል፡፡

የኖኅ መርከብ የእግዚአብሔር ሰዎች ከጥፋት የዳኑባት ስትሆን፣ ክርስቲያኖችን ከባሕረ እሳት፣ ከሞተ ነፍስና ከግብርናተ ዲያቢሎስ የምታድን የ ቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት፡፡ ዘፍ.6÷1-22፣ ም.7÷1-24፣ ም.8-1-21፡፡

## 2ኛ. ክህነተ መልከጼዴቅ

መልከጼዴቅ የሳሌም ንጉሥ፣ የእግዚአብሔር ካህን በመባል የሚታወቅ ታላቅ አባት ነው፡፡ ይህ ሰው አብራምን /አብርሃም/ ባገኘ ጊዜ ኅብስትና ወይን አቅርቦ አብራምን ባርኮታል፡፡ አብራምም ለዚሁ ታላቅ ካህን ካለው ሁሉ አሥራት አበርክቶለታል /ዘፍ.14÷18-20/፡፡

ካህኑ መልከጼዴቅ፣ የሰያሜ ካህናት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ አብርሃም ያቀረበው ኅብስትና ወይንም ዛሬ ካህናት በቤተክርስቲያን ለሚያቀርቡት መሥዋዕተ አዲስ ምሳሌ ነበር /መዝ.109/110/1-4፣ ዕብ.7÷1-28/፡፡

## 3ኛ. ቤቴል /ቤትኤል/

ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ምሥጢረ እግዚአብሔርን ያየባት ቤትኤልና በዚህ ቦታ ላይ መላእክተ እግዚአብሔር ሲወጡባት ሲወርዱባት ያየት የብርሃን መሰላል የእመቤታችንና የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት፡፡ ዛሬም መላእክተ እግዚአብሔር የምእመናንን ጸሎትና ትሩፋት ይዘው ወደ እግዚአብሔር ይወጣሉ ይወርዳሉና፡፡ ምእመናንን በረድኤት ለመጠበት ከመውጣት ከመውረድ አላቋረጡምና፡፡

## 4ኛ. ደብረ ሲና

ደብረ ሲና ሙሴ 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ ጸልዮ ሕገ እግዚአብሔር የተጻፈበትን ጽላት የተቀበለበት፣ እሥራኤል ዘሥጋ ሕገ



www.eotc-mkidusan.org

እግዚአብሔርን ጠብቀው ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉባት ተራራ ስትሆን፣ እሥራኤል ዘነፍስ /ክርስቲያኖች/ በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ተወልደው ውሉደ እግዚአብሔር የተባሉባት ርስተ እግዚአብሔር መንግሥተ ሰማያትን ለሚወርሱባት ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት /ዘጸ.24÷12-18፣ ም.31/::

## 5ኛ. ደብተራ ኦሪት

ደብተራ ማለት ድንኳን ማለት ነው፣ ደብተራ ኦሪትም ታቦተ ሕግ የኖረባት፣ ሌዋውያን ሕግ የተማሩባትና ሥርዐተ አምልኮ የፈጸሙባት ድንኳን ናት:: በዚህ ድንኳን ሰውና እግዚአብሔር ይገናኙባት ስለነበር መገናኛ ተብላለች /ዘጸ.33÷7-10/::

ደብተራ ኦሪት በሙሴ ዘመን በብዙ ጌጥ የተሠራች ነበረች:: ነቢዩ ዳዊትም ታቦት አኑሮባት ለ480 ዓመታት አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች /2ኛ ሣሙኤል 6÷3-23፣ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 16÷1-2፣ ዕብ.8፣ 9 እና 10 ይመልከቱ/:: እሷም የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት::

## 6ኛ. ቤተመቅደስ ምኩራብ /ሲናጎግ/

ምኩራብ እንደ ደብተራ ኦሪት ሁሉ እግዚአብሔር የተመለከበት ሕንፃ ነው:: ምኩራብ የተሠራው ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ956 /በ4544 ዓመተ ዓለም/ በሰሎሞን ነበር::

ነብዩ ዳዊት ቤተመቅደስን ለመሥራት ብዙ ጊዜ ቢመኝም ቤተመቅደሱ በእሱ እጅ እንዲሠራ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልነበረ ቤተመቅደሱ የሚሠራበትን ቁሳቁስ ሁሉ አሰባስቦ ለልጁ ለሰሎሞን አስረክቦታል:: /2ኛ.ሣሙኤል 7÷1-18፣ ነገሥት 5÷3-17፣ ዜና መ ቀ. 17÷1-4::

ቤተመቅደሱ እግዚአብሔር በፈቀደለት በዳዊት ልጅ በሰሎሞን እጅግ ባማረና በተዋበ አሠራር ከተሠራ በኋላ ሰሎሞንና ካህናተ ኦሪት ለብዙ ዘመናት በድንኳን ትኖር የነበረችውን ታቦተ ሕግ ከጽዮን ከተማ አምጥተው ወደ ምኩራቡ አስገቡዋት:: ምኩራቡም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠቱን ቀጠለ /መጽሐፈ ነገሥት ቀ.6÷37 ም.8-1-10:: ዜና መዋ. ምዕራፍ 3፣4 እና 5 በሙሉ/:: ይህ አስደናቂ የነበረ ቤተመቅደስ 370 ዓመታት አገልግሎት ከሰጠ በኋላ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ586 /በ4914 ዓመተ ዓለም/ በናቡከደነጾር እሥራኤላውያን ወደ ባቢሎን በተማረኩበት ጊዜ ተመዘበረ፣ ተቃጠለ፣ ፈረሰ:: የኢየሩሳሌም ከተማ በጠቅላላ ተደመሰሰች /መጽሐፈ ነህምያ.ቀ.24÷10-14 ም.25÷8-21/::

እሥራኤል ከመጡ በኋላም ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ537/በ4963 ዓ.ም. በዘሩባቤል ዘመን ተጀምሮ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ516/በ4984 ዓ.ም. ሥራው ተጠናቋል ዕዝ.3÷1-9፣ ዘካ.4÷6-10፣ ዮሐ.10÷22/::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ኢትግበሩ ቤተአቡየ ቤተ ምሥያጥ» ብሎ ሻጮችንና ለዋጮችን ያባረረበት፣ «ይህን



www.eotc-mkidusan.org

ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አስነሣዋለሁ ሲል» ስለሰውነቱ ቤተመቅደስነት የተናገረበት ቤተመቅደስ ነበር ማቴ.21÷12-13፣ ዮሐ.2÷14-22/ ቤተመቅደሱ፣ በ70 ዓ.ም. በጥጦስ ዘመን ለመጨረሻ ጊዜ ተደምስሷል፡፡

እንደዚህ ሲባል ግን ምኩራብ አንድ ብቻ ነበር ማለት አይደለም፡፡ ከዘሩባቤል በኋላም በእነሄሮድስ አግሪጳስ ሌላ ምኩራብ እንደተሠራና ሌሎች ምኩራቦች እንደነበሩ ይታወቃል /ማቴ.4÷23፣ ም9÷35/፡፡

## የቤተክርስቲያን አመሠራረት

አማናዊ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው ግንቦት 18 ቀን 33 ዓ.ም. እንደሆነ ተጽፏል፡፡ ጊዜውም በበዓለ ሃምሳ ነበር፡፡

በዚሁ ጊዜ የበዓለ ሃምሳን በዓል ለማክበር ቤተ እግዚአብሔርን ለመሳለም በመጡት አይሁድ መካከል፣ በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ተቀምጠው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ለመልበስ በተስፋ ይጠብቁ ለነበሩት ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ኃይልን ሰጣቸው /የሐዋ.2÷1-5/፡፡

ከዚህ በኋላ ሐዋርያትም በየሀገሩ ቋንቋ ይናገሩ ጀመር፡፡ በዚሁ ቀን በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት 3000 /ሦስት ሺህ/ ሰዎች አምነዋል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ መውረድ ሦስት ጥቅሞች አስገኝቷል፡፡ ይኸውም፡-

1ኛ. ለሐዋርያት ድፍረትንና መታደስን ኃይል መንፈሳዊን ሰጠ

2ኛ. በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት 3000 ሕዝብ ለማሳመን አስቻለ

3ኛ. ያመነው ሕዝብ በየሄደበት ሁሉ ወንጌልን ለመስበክ ለማስተማር ለመመስከር በቃ /የሐዋ.2÷37-41/፡፡ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ጌታውን አሳልፎ በሰጠ በይሁዳ ምትክ ሐዋርያ ለመሾም ማትያስንና ዮሴፍን መርጠው እንዲህ ብለው ጸለዩ፡፡ «የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ሥፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ሥፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው» ዕጣም ተጣጣሉባቸው፡፡ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ፡፡ የሐዋ.1÷21-26፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው የሐዋርያት ሲኖዶስ ነበረ ማለት ነው፡፡

ሐዋርያት በኃይለ መንፈስ ቅዱስ እየበረቱ ስብከታቸውን በማስፋፋታቸው «ማኅበረ እስጢፋኖስ» ተመሠረተ፡፡ ቅንዐት ሰይጣናዊ ያነሣሣቻቸው አይሁድ ግን እስጢፋኖስን በመግደል ማኅበረ እስጢፋኖስን አፈረሱ፣ ሐዋርያትን አሠሩ፤ ማኅበረ እስጢፋኖስም በየሀገሩ ተበታትነው ቤተክርስቲያንን አስፋፉ /የሐዋ.7÷57-68፣ 8÷1-17፡፡

ከዚህ ሌላ አስደናቂው ነገር ቤተክርስቲያንን ያሳድድ የነበረው ሳውል ወደ ክርስትና እምነት ተመልሶ ጠንካራ ሐዋርያ መሆኑና በጠንካራው ስብከት ቤተክርስቲያንን መገንባቱ ነው /የሐዋ.9÷1-31/፡፡ ይኸውም



www.eotc-mkidusan.org

ከ33-34 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነበር። ቤተክርስቲያን በሐዋርያት ስብከት እያደገች መሄድዋንና ደቀመዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን መባላቸውን እንገነዘባለን። /የሐዋ.11÷25-26/።

ሐዋርያትም ስብከታቸውን እያስፋፉ ብዙ አሕዛብ በማሳመን ማኅበረ ምእመናንን በማብዛት ላይ ሳሉ ቢጽ ሐሳውያን/ሐሰተኛ ወንድሞች/ የሚባሉ የቤተክርስቲያን ሰዎች በመምሰል ሐዋርያት ካስተማሩት ትምህርት ሌላ እንክርዳድ እየዘሩ ካልተገረዛችሁ ጥምቀት አይጠቅማችሁም እያሉ ምእመናንን ያስቸግሩ ነበር የሐዋ.15÷1-5።

ሐዋርያትም የእነዚህን መናፍቃን ትምህርት ከሰሙ በኋላ በ50 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም በመሰብሰብ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቤተክርስቲያን የምትመራበትን ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ ሠሩ፡ /የሐዋ.15÷6-29/።

ቤተክርስቲያናችን አንዱን ፈተና ስታልፍ ሌላ ፈተና ከፊትዋ ይደቀናል። ሐዋርያት እየታሠሩ በሰይፍ እየታረዱ ከአገር እየተሰደዱ ፀዋትወ መከራውን ታግሠው የተነሡባቸውን መናፍቃን በኃይለ እግዚአብሔር ድል ከነሡ በኋላ የመንግሥትን ሥልጣን መከታ ያደረጉ ዓላዋውያን ነገሥታትና መሳፍንት ተነሡባቸው። ከ64-312 ዓ.ም. ከኔሮን እስከ ዲዮቅልጥያኖስ ድረስ ታላቅ መከራና ስደት በክርስቲያኖች ላይ ተፈጸመ። አብያተ ክርስቲያናት ተዘጉ፤ መጻሕፍት ተቃጠሉ። የክርስትና እምነት እንዳይሰበክ ፈጽሞ ተከለከለ፤ ምእመናን ፈጣሪያቸውን አውቀው የሚድኑበትን እምነት ከመከተል ተከለከሉ፤ ክርስቶስንም የመከተል መብት ተነፈጋቸው። የሮማ ነገሥታትና መሳፍንት በክርስቲያኖች መከራና ስቃይ የሚዝናኑበት ጊዜ ነበር። ምእመናንን ከተራቡ አናብስት ማታገል፣ ከጋለ የብረት አልጋ እያስተኙ በሕይወታቸው ሲጠበሱ ማየት፣ አንበሳ ሲቦጫጭቃቸው መመልከት በዘመኑ ለነበሩ አላውያን ታላቅ የመንፈስ ርካታ የሚሰጥ ነበር። ለክርስቲያኖች ግን የመንፈስ ጥንካሬና ብርታት ሆነ።ምንም ስቃይ ቢጸናባቸው ሥርዓተ አምልኮአቸውን ከጉድጓድ ውስጥ ያከናውኑ ነበር።

በአጠቃላይ ከ64-312 ዓ.ም ያለው ዘመን ዘመነ ሰማዕታት በመባል ይታወቃል። ተባርዮ የማያስቀር አምላክ እግዚአብሔር ከዚህ ሁሉ ስቃይና መከራ በኋላ መምለኬ እግዚአብሔር ንጉሥ ቆስጠንጢኖስን በ4ኛው ክፍለ ዘመን አስነሣ። አብያተክርስቲያናት ተከፈቱ፣ መጻሕፍት ተተረጐሙ፣ ሰላም ተሰበከ፣ ሰላም ሰፈነ፣ የክርስትና ሃይማኖት ተስፋፋ።

## ዘመነ መናፍቃን

በዘመነ ሰማዕታት የክርስቲያኖችን ደም እንደጐርፍ ፈሰሰ፣ ሕይወት እንደ ቅጠል ረገፈ፣ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ኃይል አሸናፊ ከሆነች በኋላ ሰላም ተገኘ ቢባልም ያለደም ሰማዕትነትን የሚጠይቅ ዘመነ መናፍቃን ተከትሎ መጣ።

መናፍቃኑ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከትምህርተ ሐዋርያት ውጭ የሆነ የየግላቸው ፍልስፍናና አስተያየት እያመጡ በትምህርተ መለኮት ላይ



www.eotc-mkidusan.org

በመከለሳቸው ኑፋቄያቸውን ለማስወገድና ምእመናንን ለማረጋጋት በቤተክርስቲያን አባቶች ዐበይት ጉባኤያት ተደርገው መናፍቃ ተወግዘዋል።

# ዐበይት ጉባኤያት

## 1ኛ. ጉባኤ ዘኒቂያ

እለ እስክንድሮስ መንበረ ማርቆስን ተረክቦ የእስክንድርያን ቤተክርስቲያን ይመራ በነበረበት በ318 ዓ.ም. አርዮስ የሚባል መናፍቅ ተነሣ። የአርዮስ ክሕደት፣

1. ክርስቶስ ዓለም ሳይፈጠር አልነበረም፣
2. ባሕርዩ ከአብ ያነሰ ነው፣
3. የተፈጠረ እንጂ ከአብ የተወለደ አይደለም፣
4. በመጀመሪያው ዓለሙን ይፈጥርበት ዘንድ እግዚአብሔር እሱን ፈጠረው፣ እሱም ዓለምን ፈጠረ፣ በአጠቃላይ ወልድ በባሕርየ መለኮቱ ፍጡር ነው የሚል ነበር።

በዚሁ የአርዮስ ክሕደት ምክንያት በታናሽዋ እስያ በምትገኝ በኒቂያ ከተማ በ325 ዓ.ም. ጉባኤ ተከፈተ። የጉባኤው ሰብሳቢ የእስክንድርያው ፓትርያርክ እለእስክንድሮስ ሲሆን 318 ርቱዐነ ሃይማኖት አበው ተሰበሰቡ። በዚህ ጊዜ ታላቅ ታሪክ ያለው የወቅቱ ወጣት ሊቀ ዲያቆናት አትናቴዎስ የጽርዕን ቋንቋ በሚገባ ያውቅ ስለነበረ አርዮስን ተከራክሮ መልስ አሳጣው።

ቅዱስ አትናቴዎስ በኢሳ.45÷21፣ በማቴ.1÷2 በማቴ.1÷22፣ በዮሐ.1÷1–14 ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እየተነተነ፣ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደ፣ በኋላም የሰው ልጆችን ለማዳን ከቅድስት ድንግል የተወለደ፣ ቅድመ ዓለም የነበረ፣ አምላክ ወልደ አምላክ፣ በመለኮቱ ከአብ ጋር ትክክል መሆኑን አስረዳ። አርዮስም መልስ አጥቶ ተረታና በተጠቀሱት የጉባኤው አበው ተወገዘ። በዚህ ጊዜ የወልድን አምላክነት የሚያረጋግጥ፣ ጸሎተ ሃይማኖት በመባል የታወቀው ሕገ ሃይማኖት ተሠራ።

## 2ኛ. ጉባኤ ዘቁስጥንጥንያ

የኒቂያው ጉባኤ አርዮስን ተከራክሮ ረትቶ ድል ከነሣና ከወሰነ ከ56 ዓመታት በኋላ መቅዶንዮስ የሚባል ከሐዲ መንፈስ ቅዱስ ሕፁፅ የሚል የክሕደት ትምህርቱን ይዞ ተነሣ። ይህን ጉዳይ ለማየት በግንቦት ወር 381 ዓ.ም. 150 አበው ሊቃውንት ተሰበሰቡ። ጉባኤውን በመሪነት ፍጻሜ እንዲያገኝ ያደረገው አባት የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ጢሞቴዎስ ሲሆን የመቅዶንዮስ ክሕደት መሠረት የሌለው ከንቱ አባባል መሆኑን በኢሳ.6÷1-30፣ በማቴ.28÷19 በዮሐ.15÷26 ያለውን በሌላም ቃለ መጻሕፍት አስረጅነት ተከራክረው ረቱት። ጉባኤውም ከክሕደቱ ሊመለስ



www.eotc-mkidusan.org

ያልፈቀደውን መቅዶንዮስን ካወገዘ በኋላ «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ» የሚል ሕገ ሃይማኖት ሠርቶ ተፈጸመ።

## 3ኛ. ጉባኤ ዘኤፌሶን

የቁስጥንጥንያው ጉባኤ በእግዚአብሔር ኃይል መቅዶንዮስን ድል ነሥቶ ሕግ ሠርቶ፣ ሃይማኖት አቅንቶ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ካስፋፋ በኋላ በ431 ዓ.ም. ሁለት ባሕርይ ባይ ንስጥሮስ ተነሣ። ንስጥሮስ ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ልትባል አይገባም። ክርስቶስም የአብ ልጅ የማርያም ልጅ፣ የማርያም ልጅ የአብ ልጅ አይባልም በማለት ክርስቶስን ዕሩቅ ብእሲ ብሎ ካደ። ክሕደቱንም አስተማረ።

የመናፍቁ አደገኛ ክሕደት ያልተማረውን ቀርቶ የተማሩትንም ሊያሳስት የሚችል አደገኛ ፍልስፍና ስለነበር በ431 ዓ.ም. 200 ሊቃውንት በተገኙበት በኤፌሶን ጉባኤ ተሠራ። የዚህ ታላቅ ጉባኤ መሪ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር። በዚህ ጉባኤ ላይ ከቅድስት ድንግል የተወለደው ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉትን በማቅረብ ንስጥሮስን ለማሳመን ብርቱ ጥረት ተደረገ። ዮሐ.1÷14። ገላ.4÷5። 1ኛ ጢ ሞ.3÷16። ንስጥሮስ ግን ከክሕደቱ ስላልተመለሰ በጉባኤው ተወግዞ ተለየ።

በዚሁ ታላቅ ጉባኤ የንስጥሮስን ክሕደት ድል የነሣ ሊቅ ቅዱስ ቄርሎስ ነበረ። ቅዱስ ቄርሎስ በትምህርተ ሃይማኖት የበቃ የጽርዕ ቋንቋን ጠንቅቆ ያወቀ ሊቅ በመሆኑ የንስጥሮስን ተንኮል በቀላሉ መቋቋም ችሏል። በዚህም መነሻነት ስለምሥጢረ ሥጋዌ በስፋትና በጥልቀት የጻፈ ታላቅ ሊቅ ነው። ለዚህም «የሃይማኖት ዓምድ» «የዓለም ብርሃን» «የመናፍቃን መዶሻ» የሚል ቅጽል ተሰጥቶታል።

## የመናፍቃን ከቤተክርስቲያን ተለይቶ መውጣት

ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ቤተክርስቲያን፣ ምንም ፈተና ቢጸናባትም በእግዚአብሔር ኃይል ጠላቶችዋን ድል እየነሣች በሐዋርያት ትምህርት ጸንታ «አሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን» በመባል እስከ 450 ዓ.ም. ድረስ አንድነትዋን አጽንታ ቆየች። ነገር ግን የመናፍቃን ዐመጽ እየዋለ እያደረ በቤተክርስቲያኒቱ ላይ ችግር ፈጠረ። ሁለት ባሕርይ ባዩ ንስጥሮስ ያስተማረውን የክሕደት ትምህርት አጠፋለሁ ሲል አውጣኪ የሚባል መነኩሴ ተነሣ። አውጣኪ የንስጥሮስን ሁለት ባሕርይ ትምህርት አጠፋለሁ ሲል «አካላዊ ቃል ሥጋን ሲዋሐድ ባሕርየ መለኮቱ ባሕርየ ትስብእቱን ለውጦታል። ትስብእትና መለኮት ተቀላቅለዋል። ስለሆነም የክርስቶስ አካል ሕመም መከራ የማይሰማው ረቂቅ አካል በመሆኑ አንድ ባሕርይ ይባላል» በማለት የተዋሕዶን ትርጉም የሚቃረን አዲስ ክሕደት ፈጠረ።

በዚህ ጊዜ የሁለት ባሕርይ እምነት ተከታይ የሆነ ፍላብያኖስ የተባለ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ አወገዘው። አውጣኪም ክሕደቱን ደብቆ



www.eotc-mkidusan.org

«ፍላብያኖስ ያለኃጢአቴ አወገዘኝ» ብሎ ወደ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ አመለከተ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስም ጉባኤ ሠርቶ የአውጣኪን ሁኔታ መረመረ፣ አውጣኪ ግን አሁንም «እኔ 318 ርቱዐነ ሃይማኖት የወሰኑትን እቀበላለሁ፣ በሐዋርያት ትምህርት አምናለሁ፣ ቱሳሔ ብዬ ማስተማሬ ፈጽሞ ትዝ አይለኝም ሲል» ለጉባኤ አሰማ።

ቅዱስ ዲዮስቆሮስም «አንድ ባሕርይ ማለት ባሕርየ መለኮት ባሕርየ ትስብእትን ሳይ ቋጒን ሳያጠፋ ሳይለውጥ፣ ባሕርየ ትስብእት ባሕርየ መለኮትን ሳይለውጥ በባሕርየ መለኮት ሕፀፅ ሳያስከትል፣ አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ከነፍስዋ ነፍስ ከሥጋዋ ሥጋ ነሥቶ በፍጹም ተዋሕዶ መወለዱን፣ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ታምናለህን?» ብሎ ጠየቀው። እሱም «አዎን አምናለሁ» ብሎ በጸሎተ ሃይማኖት እምነቱን ለጉባኤው ገለጸ። ጉባኤውም የአውጣኪን አባባል ከሰማ በኋላ ፍላብያኖስን አስጠርቶ ጠየቀው እርሱም አንድ አካል ሁለት ባሕርይ በሚል ትምህርት የሚጸና መሆኑን አረጋገጠ። ጉባኤውም የፍላብያኖስን ከክሕደቱ አለመመለስ ካረጋገጠ በኋላ፣ አውጣኪን ወደ ሥራው መልሶ ፍላብያኖስን አውግዞ ለየ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፍላብያኖስን ወደ ሮማው ፓትርያርክ ወደ ቀዳማዊ ልዮን አቤቱታውን ቀጠለ። በልዮንና በዲዮስቆሮስ መካከል ቅራኔ ተመሠረተ። ከዚህ በኋላ ነበር «ጉባኤ ከለባት» /የውሾች ጉባኤ/ የሚባለው የኬልቄዶን ጉባኤ በ451 ዓ.ም. የተካሄደው። ዲዮስቆሮስ የማስረዳት መብት ተነፍጎት በቤተ መንግሥት ኃይል አስገዳጅነት በግፍ ተጋዘ፣ ኢሰብአዊ ድብደባም ጥርሶቹ ረገፉ። በዚህ ሁሉ ፍትሕ አልባ ድርጊት፣ የአባቶቹ የሐዋርያትን ጽዋዕ በመቀበል እውነተኛ ሐዋርያነቱን አስመሰከረ። ከዚህ በኋላ በትምህርተ ሐዋርያት፣ በደመ ሰማዕታት በአንድነትዋ ጸንታ ከኖረችው አሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ባዮች ተለይተው መጡ።

የኬልቄዶን ጉባኤ ፍትሕ የጠፋበት፣ ግፍ የተፈጸመበት የዐመፅ ጉባኤ በመሆኑ ቤተክርስቲያናችን አልተቀበለችውም፤ እንዲያውም ጉባኤ ከለባት/የውሾች ጉባኤ/ ጉባኤ አብዳን/ የእብዶች ጉባኤ/ብላ ሰይማዋለች።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን ማለት በ1517 ዓ.ም. ሉተር ማርቲን የተባለ ካቶሊካዊ መነኩሴ የሮማን ጳጳሳትና ሥርዓት በመቃወም ተነሣ፤ እሱም ከነበረበት ገዳም ብዙ መነኮሳትንና መነኮሳይያትን አስከትሎ በመውጣቱ በፕሮቴስታንቶች እና በካቶሊኮች መሐል ለ100 ዓመታት ያህል ጦርነት ተካሂዷል።

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ

ኢትዮጵያ አምልኮተ እግዚአብሔር የተፈጸመባት ጥንታዊትና ቅድስት ሀገር ናት። በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ እና በዜና መዋዕል ካልእ እንደምንረዳው የሳባ ንግሥት፣ የቀዳማዊ ምኒልክ እናት ንግሥት ማክዳ የሰሎሞንን ጥበብ ባየች ጊዜ ከተናገረቻቸው ኃይለ ቃላት ውስጥ



www.eotc-mkidusan.org

«በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ንጉሥ እንድትሆን በዙፋኑ ላይ ያስቀምጥህ ዘንድ የወደደህ አምላክ እግዚአብሔር ቡሩክ ይሁን..» በማለት ለሰሎሞን ጥበብን የሰጠ ፈጣሪዋን ስታመሰግን እንመለከታለን መጽ.ነ.ቀዳ 10÷1-10፣ ዜና መ ካል.9÷1-8::

ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ950 ዓ.ዓ /በ4550 ዓ.ዓ/ ገደማ ቀዳማዊ ምኒልክ በሌዋውያን አጃቢነት ታቦተ ጽዮንን ይዞ ወደ አክሱም ከመጣበት ዘመን ጀምሮ ምኩራብ ተሠርቶ አምልኮተ እግዚአብሔር ሲፈጸም ለመኖሩ በአክሱም አውራጃ በተለይም በዐድዋ አውራጃ በየኻ ወረዳ ያለው የምኩራብ ፍርስራሽ በቂ ማስረጃ ነው::

ኢትዮጵያ ሀገራችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ80 ጊዜ ባላነሰ የመጠቀሷ ምክንያት የሥርዓተ አምልኮዋና የሥልጣኔዋ ጥንታዊነት እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይሆንም:: /ለምሳሌ መዝ.67/68/÷31፣ የሐዋ.8÷27-3.:: መመልከቱ ጠቃሚ ነው::/

ከላይ ባጭሩ እንደተገለጸው፣ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከቅድመ ክርስትና ጀምሮ ከአምልኮ ባዕድ ርቃ ፈጣሪዋን አውቃ በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ የኖረች ጥንታዊት ሀገር መሆንዋን ስንገነዘብ፣ በዘመነ ሐዲስም ቀደምትነት ካላቸው ሀገሮች ጋር በአንደኛው ምእት ዓመት ጥምቀተ ክርስትናን የተቀበለች የታሪክ ባለጸጋ ሀገር መሆንዋን ከቅዱስ መጽሐፍ ማረጋገጥ ይቻላል የሐዋ.27÷39::

በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካይነት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ ቢታወቅም ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ተሟልቶ በመላ ሀገሪቱ ስብከተ ወንጌል ሳይዳረስ እስከ 330 ዓ.ም. ገደማ እንደቆየ በልዩ ልዩ የታሪክ ጸሐፊዎች ዘንድ ተመዝግቧል::

## ሰላማ ከሣቴ ብርሃን /ቅዱስ/

ኢዛና እና ሳይዛና /አብርሃና አጽብሐ/ በነገሡ በ15ኛው ዓመት ቅዱስ ፍሬምናጦስ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን አሟልቶ ለመፈጸም የሚያስችለውን ሥልጣንና ትምህርት ለማምጣት ወደ እስክንድርያ ተላከ::

የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ቅዱስ አትናቴዎስም ከኢትዮጵያ ነገሥታት ከኢዛና እና ሳይዛና የተላከለትን ደብዳቤና ገጸ በረከት ተቀብሎ ፍሬምናጦስን የኢትዮጵያ ጳጳስ አድርጎ በመሾም መልሶ ላከው፣ ብዙ የከበሩ ንዋያተ ቅዱሳትንም ለነገሥታቱ ላከላቸው::

ፍሬምናጦስና ከእርሱ ጋር የነበሩት ኢትዮጵያዊያን ሊቃውንትም ተልእኮአቸውን ፈጽመው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ሁለቱም ወንድማማች ነገሥታት በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው:: ነገሥታቱም በሐማሴን አውራጃ በፍሬምናጦስ እጅ ተጠምቀው አብርሃ ወአጽብሐ ተባሉ:: ፍሬምናጦስ ከነገሥታቱ ጋር መላ ኢትዮጵያን እየዞረ ሕዝብን እያጠመቀ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን አስተማረ:: ለዚህም የምእመናንን ልቡና በስብከቱ አብርቷልና ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ተብሏል::



www.eotc-mkidusan.org

አብርሃ ወአጽብሃና ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ቤተመንግሥትና ቤተክህነትን አስተባብረው የሚመሩ ፍቅረ እግዚአብሔር ያደረባቸው እውነተኛ ሐዋርያት ነበሩ፡ በዘመናቸው ብዙ መጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት ከጽርዕ ወደ ግእዝ ተተርጉሟል፣ የግእዝ ፊደል አሁን ያለውን ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጓል ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንደ አክሱም ጽዮን፣ አብርሃ ወአጽብሐ፣ ተድባበ ማርያም፣ መርጦለማርያም፣ ጣና ቂርቆስ፣ ጎሐ ጽዮንና ሌሎችም አያሌ አስደናቂ የድንጋይ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል። የሀገሪቱ የሥልጣኔ መረጃ የሆኑ ሐውልቶች ቆመዋል። መጻሕፍት ከጽርዕ ወደ ግእዝ በሰላማ ከሣቴ ብርሃን ጊዜ መተርጐማቸውን ገድለ አብርሃ ወአጽብሃ ያስረዳል።

## ተሰዓቱ ቅዱሳን

ተሰዓቱ ቅዱሳን በ5ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ከሮማና ከእስያ በምናሴ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ አባቶች ናቸው።

እነዚህ አባቶች ኢትዮጵያ ሀገራችን መካነ ቅዱሳን፣ ሀገረ እግዚአብሔር መባልዋን ከታሪኳ ያጠኑ በመኖራቸው በኬልቄዶን ጉባኤ ተወካዮች በደረሰባቸው ማሳደድ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ በአክሱም ቤተመንግሥት በቤተቀጢን በእንግድነት ብዙ ጊዜ ቆይተዋል። በኋላ ግን በአክሱምና በዓድዋ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ሥርዓተ ምንኩስናን በኢትዮጵያ መሥርተዋል፣ አስፋፍተዋልም።.

ተሰዓቱ ቅዱሳን፣

1. አቡነ አረጋዊ
2. አባ ገሪማ
3. አባ ጽንጠሌዎን
4. አባ ሊቃኖስ
5. አባ አፍጼ
6. አባ ጽሕማ
7. አባ ጉባ
8. አባ አሌፍ
9. አባ ይምአታ የሚባሉ ሲሆኑ በተለይም አቡነ

«አረጋዊ የኢትዮጵያ መነኮሳት አባት በመባል ይታወቃሉ። በስማቸው የታነጸው ታሪካዊ ቤተክርስቲያን በትግራይ ክፍለ ሀገር በደብረ ዳሞ ገዳም ይገኛል።

## ቅዱስ ያሬድ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በዓለም ደረጃ ስመ ጥሩ በሆነው ንጉሥ በኢዛና /በአብርሃ/ ዘመን ሥርዓተ ክርስትናን ስታስፋፋ ዝናዋ በዓለም በይበልጥ የገነነ ሆነ። ይልቁንም በ505 ዓ.ም. የተወለደው ቅዱስ ያሬድ የኢትዮጵያን የታሪክ ዕድገት የሚገነባ ታላቅ ሥራ አከናወነ።



www.eotc-mkidusan.org

ይህ ታላቅ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በ505 ይስሐቅና ክርስቲና ከሚባሉ ደጋግ ሰዎች በትግራይ ክፍለ ሀገር በአክሱም አውራጃ ተወለደ::

ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ፣ የፊደልን ቅርጽ ለይቶ ንባብ ለማወቅ ከሰባት ዓመት ያላነሰ ጊዜ ወስዶበት እንደነበረ ቢታወቅም ተስፋ ሳይቆርጥ ፈቃደ እግዚአብሔርን እየጠየቀ ጥረቱን ቀጠለ:: እግዚአብሔርም የልቡን ቅንነትና ትጋቱን ተመልክቶ 24ቱ ካህናተ ሰማይ የሚዘምሩትን ሰማያዊ ዜማ ገለጸለት:: ከገነትም ሦስት አዕዋፍ ተልከው ጣዕመ ዜማውን አሰሙት:: ስለዚህ ነው ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ዜማውን ሲቃኝ፣ «ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ግናይ» በማለት አድናቆቱን በተመስጦ የገለጸው::

ቅዱስ ያሬድ በኃይለ መንፈስ ቅዱስ እየተመራ ዓለም የሚደነቅበትን፣ እኛ ኢትዮጵያዊያን የምንገለገልበትንና የምንኮራበትን ዜማ፣ በግእዝ በአራራይና በዕዝል ደርሶ የዜማውን ልክ ለማወቅ የሚያስችለንን ምልክት አበጅቶ አስረክቦናል::

ቅዱስ ያሬድ በዜማና በቅኔ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን መጻሕፍተ ብሉያትን፣ ሐዲሳትንና ሊቃውንትን ጠንቅቆ ያወቀ ታላቅ ሊቅና ፍጹም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አባት መሆኑን የዜማው መጻሕፍት በግልጽ ይመሰክሩለታል:

ቅዱስ ያሬድ ሲዘምር ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንስሳትም ጣዕመ ዜማውን በልዩ ተመስጦ ያዳምጡለት እንደነበር በብዙ ሊቃውንት አንደበት ይነገራል:: /ለዚህም በጊዜው የነበሩ የአጼ ገብረ መስቀልን ታሪክ ማስታወስ በቂ ማስረጃ ነው::/

አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎችና ተናጋሪዎች ቅዱስ ያሬድን ኢትዮጵያዊ አይደለም ለማስባልና ዜማውንም ከሌላ /ከውጭ/ ተምሮታል ለማለት ሲሞክሩ ኖረዋል:: ይህም የሆነው:-

1ኛ. እንደዚህ የመሰለ ሊቅ በአፍሪካ ውስጥ ሊገኝ አይችልም ለማለት፣

2ኛ. ከሌላ ቤተክርስቲያን ጋር ግንኙነት የነበረው በማስመሰል ታሪክን ለመሻማት የሚደረግ መላምት የታሪክ አጻጻፍ እንጂ ቅዱስ ያሬድ ተራ ደራሲ ነበር ወይም ወደ ውጭ ሄዶ ከእገሌ ቤተክርስቲያን ጋር ግንኙነት ነበረው የሚል ታሪካዊ ማስረጃ የለም፤ በቤተክርስቲያናችንም አልተጻፈም::

ቅዱስ ያሬድ መንፈስ እግዚአብሔር ያደረበት፣ ዜማውም ጸሎትና የእምነት ማረጋገጫ ስለመሆኑ ከራሱ ጸዋትወ ዜማ የበለጠ ማስረጃ ሊኖር አይችልም:: /ገድለ ያሬድንና ገድለ አብርሃ ወአጽብሐን ተመልከት::/

## ጳጳስ ለማግኘት የነበረ ችግር

ቤተክርስቲያናችን ፍሬምናጦስን በራስዋ ፈቃድ ያሾመች ቢሆንም ከአቡነ ሰላማ በኋላ ግን በእስክንድርያው ፓትርያርክ ፈቃድ ግብጻውያን ይሾሙ ስለነበር ለመላ ኢትዮጵያ አንድ ጳጳስ ለማግኘት ከፍተኛ ችግር

ነበረባት። በተለይም የግብፅ መንግሥት እስላም በመሆኑ በኢትዮጵያና በግብፅ መንግሥታት መካከል የፖለቲካ ውዝግብ በተነሣ ቁጥር ቤተክርስቲያናችንም ጳጳስ ለማግኘት ከፍተኛ ችግር ነበረባት።

## ቤተክርስቲያናችን በዘመነ ዮዲት /ጉዲት/

ዮዲት በ842 ዓ.ም. የአክሱሙን ንጉሥ የድግናዣን ልጅ አንበሳ ውድምን ድል ነሥታ የኢትዮጵያን መንግሥት የያዘች ናት። ዮዲት ትውልደ ነገድዋ ከፈላሾች ስትሆን በክርስትና ሃይማኖት ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያደረባት 40 ዓመት ሙሉ የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥፋት የሞከረች ነበረች። ስለሆነም በቤተክርስቲያናችን ላይ ይህ ነው የማይባል ጥፋትና ግፍ ተፈጸመ። ካህናት እንደበግ እየታረዱ አለቁ፤ አብያተ ክርስቲያናት ተ ቃጠሉ፤ መጻሐፍት ጠፉ፤ ተቆነጻጸሉ። ሐውልቶች ተሰባበሩ፤ 40ው ዓመት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የስደትና የመከራ ጊዜ ነበር። ታቦተ ጽዮን ግን ከአክሱም ተሰዳ በዝዋይ ደሴት ከጥፋት ዳነች።

**አፄ ቅዱስ ላሊበላ፡-** ኢትዮጵያ የዮዲትን 40 የፈተና ዓመታት ካሳለፈች በኋላ ቤተክርስቲያናችን ከ11ኛው ምእተ ዓመት ጀምራ ታሪክዋን ስታድስ እንመለከታለን። በላስታ ዘመነ መንግሥት እንደ ጥንቱ አብያተ ክርስቲያናት ታነጹ። በእነቅዱስ ሐርቤ /ገብረ ማርያም/ና በእነ ቅዱስ ላሊበላ ዘመን ቤተክርስቲያናችን አዲስ ዕድገት አሳየች። በቅዱስ ላሊበላ የተሠሩ የድንጋይ ውቅር አብያተክርስቲያናት ዛሬም ድረስ በዓለም ደረጃ ቤተክርስቲያናችንና ሀገራችንን የሚያኮሩ ሆነዋል።

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በዚህም ዘመን ጳጳስ ለማግኘት ብዙ ችግር ቢያጋጥምም ከብዙ ጥረት በኋላ ተፈላጊውን መንፈሳዊ አባት ማግኘት ተቻለ።

## አቡነ ተክለ ሃይማኖት

የመንግሥት ሥልጣን ከላስታ ወደ ሸዋ ሲዛወር በአጼ ይኩኖ አምላክ ጊዜ ስብከተ ወንጌልን በመሀል አገር በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ ያዳረሱ ታላቅ ሐዋርያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተነሡ።

አቡነ ተክለሃይማኖት በወሎ ክፍለ ሀገር በሐይቅ ገዳም በትግራይ ክፍለ ሀገር በደብረ ዳሞ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ከፈጸሙ በኋላ ብዙ አረማውያንን ከክሕደት ወደ እምነት የመለሱ አባት ከመሆናቸውም ሌላ አጼ ይኩኖ አምላክን በማሳመን ለቤተክርስቲያን ማደሪያ የሚሆን ርስት አስፈቅደዋል።

## አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

ከ1358-1417 ድረስ የነበሩት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ከተነሡ የያሬድ ደቀ መዛሙርት 8ኛ ደቀመዝሙር ናቸው። እኒህ አባት የፀዋትወ ዜማ ባለሙያ ታላቅ ሊቅ ከመሆናቸውም



www.eotc-mkidusan.org

ሌላ ተደናቂነትን ያተረፉ ከ40 በላይ የነገረ ሃይማኖት መጻሕፍት ጽፈው ለቤተክርስቲያን አስረክበዋል፡፡ የ15ኛው ክፍለ ዘመን ሐዋርያ ሲሆኑ ቤተክርስቲያናችን ከምትገለገልባቸው የእሳቸው ድርሰቶች መካከል ሰዓታትና አርጋኖንን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አባ ጊዮርጊስ በነገረ ሃይማኖት ትምህርት የተራቀቁ ስለነበሩ «ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ» የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡ የአባ ጊዮርጊስ አብዛኛዎቹ መጻሕፍት እስካሁንም ወደአማርኛ አልተተረጎሙም፡፡

## ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከ1434-1468 ዓ.ም. ድረስ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት ናቸው፡፡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ቤተክርስቲያንን የበለጠ እንድትጠናከር መንፈሳዊ ቅንዓት ስለነበራቸው እንደ አባቶቻቸው እንደ አብርሃ ወአጽብሐ እንደነቅዱስ ላሊበላ ቤተመንግሥትን ከክህነት ጋር አስተባብረው ያስተዳድሩ ነበር፡፡

በዘመናቸው መጻሕፍት በብዛት ተጽፈዋል፣ በዓላት በብዛት እንዲከበሩ ተደርገዋል፡፡ በተለይም እመቤታችንን ከልብ የሚወዱ ስለነበረ በዓመት ውስጥ 33 የእመቤታችን በዓላት እንዲከበሩ የደነገጉ እሳቸው ናቸው፡፡

ሌላው ለቅድስት ድንግልና ለመስቀል መስገድ አይገባም የሚሉ እስጢፋኖስና በርተሎሜዎስ የሚባሉ መነኮሳት ቢነሡባቸውም የእነዚህን መናፍቃን ባሕል የሚከተል ክርስቲያን እንዳይኖር በጽኑ አስተምረዋል፡፡

በአጠቃላይ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ሃይማኖታቸውን የሚወዱ ቤተክርስቲያናቸውን የሚጠብቁ ታላቅ ንጉሠ ነገሥት ስለነበሩ «ዳግማዊ ቆስጠንጢኖስ» የሚል የክብር ቅጽል በቤተክርስቲያን ዘንድ አግኝተዋል፡፡

## ቤተክርስቲያናችን በግራኝ መሐመድ ወረራ ጊዜ

ቤተክርስቲያናችን ጠላቶችዋን በኃይለ እግዚአብሔር ድል እየነሣች የታሪክ ማኅደር መሆንዋ ባይቀርም ጠላቶችዋ ያለእረፍት ከየአቅጣጫው መልካቸውን እየለዋወጡ ብቅ ማለታቸው አልቀረም፡፡ ስለሆነም በ1506 ዓ.ም. የተወለደው ግራኝ መሐመድ በ1539 ዓ.ም. በክርስቲያኖች ላይ ጦርነት ከፈተ፡፡ ግራኝ ጦርነቱን ያስነሣው በእስላሞቹ ቱርኮችና ግብጾች አቀነባባሪነትና ደጋፊነት ስለነበር ዐፄ ልብነ ድንግልን አሸንፎ ኢትዮጵያን ወረረ፡፡ በክርስቲያኖች ላይም መራራ እልቂት ደረሰ፡፡ በዘመነ ዮዲት የተፈጸመው ግፍ ሁሉ በዚህ ዘመን ተደገመ፡፡ በዮዲትና በግራኝ መሐመድ የተፈጸመ ግፍ ልዩነት ቢኖረው የግራኝ መሐመድ የግዛት ዘመን 15 ዓመት መሆኑ ብቻ ነው፡፡ ስደቱ ቃጠሎው፣ መታረዱ ግፉ ሁሉ አንድ ዓይነት ነበረ፡፡ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት፣ መፋታት፣ በየዛፉ ሥር እየተሰበሰቡ አምልኮ ባእድ መፈጸምና የመሳሰሉት መጥፎ ልምዶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ከግራኝ መሐመድ ወረራ በኋላ እንደሆነ ይነገራል፡፡



www.eotc-mkidusan.org

ቤተክርስቲያናችን ግን ይህ ሁሉ መከራ ቢደርስባትም ክርስቶስ በጽኑ ዐለት ላይ ስለመሠረታት ተሳደደች እንጂ አልጠፋችም።

ከዚህ ሁሉ ስቃይ በኋላ በ1554 ዓ.ም. የአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ገላውዴዎስ ግራኝ መሐመድን በጦርነት ገድሎ በአባቱ ዙፋን ላይ ተቀመጠ። ክርስቲያኖችም መብታቸው ተጠብቆ በሰላም መኖር ቻሉ። አብያተ ክርስቲያናትም በክብር ተገለገሉ።

## ሚስዮናውያን በኢትዮጵያ

ከ1599-1621 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ካቶሊካውያን ኃይላቸውን በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ማሳየት ጀመሩ፡ ከአጼ ሠርጸድንግል ጀምሮ በነበረው በጎንደሩ ዘመነ መንግሥት ነገሥታቱ ሃይማኖታቸው የቀና ቤተክርስቲያናቸውን የሚጠብቁ እንደ ነበር ቢታወቅም አጼ ሱስንዮስ ግን ከሮማ መንግሥትና ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዘንድ ተወዳጅነትን ለማትረፍና ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ሃይማኖታቸውን ለወጡ። ካህናትና ምእመናን ሃይማኖታቸውን ሥርዓታቸውን እንዲለውጡና በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥርዓት እንዲመሩ ተገደዱ።

ለዚህም የንጉሡን ትእዛዝ ለማስፈጸም በሰባኪነት ስም ከሮማ የተላኩ «ኢየሱሳውያን» የተባሉ ሚስዮናውያን በቤተክርስቲያናችን ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጠሩ፡ ካህናት ታሠሩ፣ ተባረሩ፡ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ተፋለሰ።

ነገር ግን ቤተክርስቲያኑን የሚጠብቅ እግዚአብሔር በአጼ ሱሱንዮስ ላይ ኃይሉን አሳየ፣ አጼ ሱሱንዮስ በጽኑ ደዌ ሲያዙ «ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ» ተባለ።

## ፋሲል ነገሠ ሃይማኖት ተመለሰ

አጼ ፋሲል የኢትዮጵያን ዙፋን ከአባታቸው ከአጼ ሱሱንዮስ ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ተፋልሶ የነበረውን ሥርዓተ ቤተክርስቲያን መልሰው አስከበሩ፡ መጻሕፍት ከግእዝ ወደ አማርኛ በአንድምታ ተተረጎሙ። ስብከተ ወንጌል ተስፋፋ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ታነጹ።

በተለይም ጎሊና ማሪኪ የሆነውን ቤተመንግሥታቸውንና ያሠሩዋቸውን አብያተ ክርስቲያናት ስንመለከት የኢትዮጵያን ጥበብ በአጼ ፋሲል አማካይነት እናደንቀዋለን። ከዚህ ቀጥሎ በነበሩ ነገሥታትም ሆነ በዘመነ መሳፍንት፣ ከዘመነ መሳፍንት በኋላም በአጼ ቴዎድሮስ፣ በአጼ ዮሐንስ በአጼ ምኒልክና በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን መጠነኛ ዕድገት በማሳየት በተመሳሳይ ሁኔታ ታሪክዋን መዝግባለች።



www.eotc-mkidusan.org

## ቤተክርስቲያናችን በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ

አጼ ኃይለሥላሴ በነገሡ በ5ኛው ዓመት ማለት በ1928 ዓ.ም. ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረባቸው አምስት ዓመታት በሀገሪቱ ላይ የተፈጸመውን ግፍ ስናስታውስ እጅግ አስከፊ መሆኑን እንገነዘባለን። ለምሣሌ:- 760,300 ኢትዮጵውያን ማለ ቋቸውን፣ 525,000 ቤቶች መ ቃጠላቸውን፣ 137,000,000 ልዩ ልዩ እንስሳት መጥፋታቸውን ስንመለከት ግፉ ምን ያህል እንደነበር መገንዘብ ያስችላል።

የሀገሪቱ ችግር ከቤተክርስቲያኒቱ ችግር ፈጽሞ ስለማይለይ ግምባር ቀደም የችግሩ ቀማሽ ቤተክርስቲያናችን ነበረች። አያሌ አርበኞች ስለሀገራቸው ነፃነት ደማቸውን ሲያፈሱ አጥንታቸውን ሲከሰክሱ ብዙ የቤተክርስቲያን አባቶችም ስለሀገራቸውና ስለ ቤተክርስቲያናቸው ክብር ሰማዕትነትን ተቀብለዋል። የአቡነ ጴጥሮስ፣ የአቡነ ሚካኤልና የሌሎችም ሊ ቃውንተ ቤተክርስቲያን ሰማዕትነት በአርአያነት ሲጠቀስ የሚኖር ሕያው ታሪክ ነው። በደብረሊባኖስ ገዳም በጅምላ የተጨፈጨፉት መነኮሳትና በዓል ለማክበር የተሰበሰቡት ምእመናንም የሚዘነጉ አይደሉም።

በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ብዙ የብራና መጻሕፍት ተዘርፈዋል፤ አያሌ የታሪክ ቅርሶችም ተወስደዋል፤ ዮዲት ከሰባበረችው ታላቅ የአክሱም ሐውልት ቀጥሎ በርዝመቱ ሁለተኛ የሆነው ሐውልታችን ተወስዶ ሮማ ላይ ተተክሏል። እንግሊዞች ከአጼ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ የዘረፏቸው የብራና መጻሕፍቶቻችን ለብሪቲሽ ሙዚየም ማዳበሪያ እንደሆኑ ሁሉ፣ በጣልያኖች የተዘረፉ መጻሕፍቶቻችንና ቅርሶቻችንም ለሮማ ቤተመጻሕፍት የታሪክ ማበልጸጊያ ሆነዋል።

## አዲስ የታሪክ ምዕራፍ

በአራተኛው ክፍለ ዘመን ከተሾመው ከአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በኋላ ይሾሙ የነበሩ ጳጳሳት ግብጻውያን እንደነበሩ ተገልጿል። ግብጻውያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ከሥራቸው ለማድረግ ሲሉ «ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሹሙ» የሚል ሕግ አውጥተው ለ1560 ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ግብፃውያን ጳጳሳት ተሾመዋል። ይኸውም አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንና ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖትን ሳይጨምር ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ በራስዋ ሊቃውንት ጵጵስና እንዲሾምላት የጠየቀችው በቅዱስ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት፣ ከዚያም በአጼ ዮሐንስ 4ኛ ጊዜ እንደነበር ተጽፏል።

ነገር ግን የሰው ሀሳብ ፍጻሜ የሚያገኘው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲጨመርበት በመሆኑ ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ማለትም:-

1ኛ. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ- የትግራይና የሰሜን ጳጳስ፣
2ኛ. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ- የወሎ ጳጳስ፣



www.eotc-mkidusan.org

3ኛ. ብፁዕ አቡነ አብርሃም- የጎጃምና የጎንደር ጳጳስ፣
4ኛ. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል- የምዕራብ ኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው በመሾማቸው በቤተክርስቲያናችን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ተከፈተ።

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን መንፈሳዊ መብቷን ከተቀዳጀችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አምስት ፓትርያርኮችን ሾማለች። እነሱም፣

1ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የተሾሙበት ጊዜ ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም.

2ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ » » ግንቦት 1 ቀን 1961 ዓ.ም.

3ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት » » ነሐሴ 23 ቀን 1969 ዓ.ም.

4ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ » » ነሐሴ 29 ቀን 1980 ዓ.ም.

5ኛ. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ » » ሐምሌ 5 1984 ዓ.ም.

ማሳሰቢያ

ዝግጅቱ ለሰንበት ት/ቤቶች መምህራን ማስተማሪያ ተብሎ ከልዩ ልዩ መጻሕፍትና እትሞች ተወጣጥቶ ባጭሩ የተቀነባበረ ነው።



www.eotc-mkidusan.org